# ደንብ

## ሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

ተዛማች ሠነዶች፡- ECM, ECMRA

ኃላፊ ጽ/ቤት፣- ዋና የሥራ ኃላፊChief Operating Officer
የመገልገያዎች አስተዳደር

**የማህበረሰቡ የፐብሊክ ስኩልስ/ የህዝብ ት/ቤቶች አጠቃቀም**

I. ዓላማ

ከማህበረሰቡ የት/ቤት መገልገያዎች አጠቃቀም ጋር የሚዛመዱ መመሪያዎችን እና ቅደም-ተከተሎችን ለማሳተም

II. የቀድሞ መነሻ

የህዝብ/ፐብሊክ ት/ቤቶችን የማህበረሰብ አጠቃቀም ማለት በሞንትጎመሪ ካውንቲ መንግስት እና በሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩል (MCPS) ስርዓት የሚቀርብ አገልግሎት ነው። በኤጀንሲዎች መካከል ትብብር ቦርድ/ Interagency Coordinating Board (ICB) የማህበረሰብን ት/ቤቶች አጠቃቀም የሚመራ እና መመሪያዎችን እና ቅደም-ተከተሎችን የሚፈቅድ የፖሊሲ ቦርድ ነው። የህዝብ/ፐብሊክ መገልገያዎችን የማህበረሰብ አጠቃቀም ጽ/ቤት / Community Use of Public Facilities office (CUPF) የ ICB አስተዳደራዊ ሀላፊነቶችን የሚወጣ ነው። የፖሊሲ ቦርዱ የተቋቋመው የህዝብ/ፐብሊክ ት/ቤቶችን የማህበረሰብ አጠቃቀምን ለማመቻቸት ነው።

የህዝብ ኤጀንሲዎች እና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ቡድኖችን፣ በካውንቲው ውስጥ ወይም ውጪ የሚገኙ የዜጎች ድርጅቶችን፣ እና የትርፍ/ንግድ ኢንተርፕራይዞችን ጨምሮ፣ የት/ቤት መገልገያዎችን መጠቀም ይችላሉ። ት/ቤቶች ለሁሉም ማለት በሚቻል መልኩ ማህበረሰብ ተኮር ተግባር ስፖንሰር ለማድረግ ወይም ለማዘጋጀት ለሚፈልጉ ሁሉ ክፍት ናቸው።

የ ICB አባላት የሚያካትቱት የካውንቲ መንግስት ዋና አስተዳደርን፣ የትምህርት ቦርድ አባልን እንደ የስራ ሀላፊነት አንፃር አባልን፣ የት/ቤቶች የበላይ ሀላፊን፣ የሞንትጎመሪ ኮሌጅ ፕሬዝዳንትን፣ የሜሪላንድ ክልላዊ ፓርክ እና የዕቅድ ኮሚሽን አባልን፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ምክር ቤት ውስጥ የምክር ቤት አባል ወይም የሰራተኞች መሪ ወይም ነባር የሰራተኛ አባልን፣ አንድ በየበላይ ሀላፊ የሚመረጥ ዜጋን፣ ይሄም በትምህርት ቦርድ ፈቃድ የሚወሰን ነው፣ በአክውንቲ አስተዳዳሪ የሚመረጡ ሦስት ዜጎች፣ በሞንጎመሪ ካውንቲ የሁለተኛ ደረጃ ዳይሬክተሮች ማህበር የሚወከል ግለሰብ፣ እንደ ስራ ሀላፊነት አንፃር አባልን፣ እና በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት አስተዳደሮች ማህበር የሚወከል ግለሰብን እንደ ስራ ሀላፊነት አንፃር አባልን ነው።

## III. መመሪያዎች

### A. ለትርፍ የማይሰሩ ተጠቃሚዎች

MCPS -- ት/ቤቱ ራሱ ከቤት ውስጥ እና ከቤት ውጪ በት/ቤት ቦታ ላይ አጠቃቀም ቅድሚያ ይሰጣል። ይሄም ማለት የት/ቤት ሰራተኞች የተያዙ ቦታዎችን ለራሳቸው ለመጠቀም ቀዳሚዎቹ ናቸው። ቦታ ለማስያዝ የት/ቤት ሰራተኞች ማስገባት ያለባቸው ከ ሴፕቴምበር 15 በፊት ነው፣ ነገር ግን የተያዘው ቀን የሚሆነ በየአመቱ ኦገስት 15 ነውልል ከ ሴፕቴምበር 15 በኋላ፣ የሚከተሉት ቡድኖች ቦታ ማስያዝ እና መጠቀም ይችላሉ፦

1. የህፃናት እንክብካቤ
2. PTA
3. ካውንቲ እና ሌሎች የመንግስት ኤጀንሲዎች
4. ለትርፍ ያልተቋቋሙ የማህበረሰብ ድርጅቶች
5. ለትርፍ ያልተቋቋሙ ካውኒቲ-መሰረት ያላደረጉ ድርጅቶች ወይም የስራ/የንግድ ኢንተርፕራይዞች

### B. የስራ/የንግድ ኢንተርፕራይዞች

ማንኛውም የትርፍ/የንግድ ኢንተርፕራይዝ (እንደ አንቀሳቃሽ ት/ቤቶች፣ SAT ዝግጅት ኩባንያዎች) ወደ CUPF ሪፈር ተደርጎ በካውንቲ ኢንሹራንስ መስፈርቶች መሰረት እንደሚሰራ መረጋገጥ አለበት።

## IV. ቅደም-ተከተሎች/ሂደቶች

A. ት/ቤቶች እንደ መማሪያ ክፍሎች፣ ጂምናዚየም፣ የኮምፒዩተር ላብራቶቺ፣ ወይም የሚዲያ ማዕከል አይነት በት/ቤት ውስጥ የሚገኙ ቦታዎች ላይ የምግብ እና መጠጦች አጠቃቀምን የሚመለከቱ የአካባቢ ፖሊሲዎችን ያዘጋጃሉ።

B. ት/ቤቶች በሁሉም የሳምንቱ ቀናት ለማህበረሰብ መጠቀሚያነት ክፍት ናቸው፣ ከትምህርት መስጫ ሰአታት ውጪ፣ ከሰአት 6:30 a.m. እስጀ 11 p.m. ድረስ። ተጠቃሚዎች የት/ቤት መገልገያዎችን በሳምንቱ መጨረሻ/እረፍት ቀናት እና በበአል ቀናት ከጠዋት 7:30 a.m. እስከ እኩለ ለሊት ድረስ እንዲጠቀሙ ተፈቅዶላቸዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ፣ ማራዘሚያዎቹ መደበኛ የት/ቤት ትምህርት ፕሮግራምን ካልገደቡ ወይም ካላቋረጡ እና መሸፈን የሚችሉ ሰራተኞች እስከአሉ ድረስ እነዚህ ሰአታት ሊራዘው ይችላሉ። ቀደም ብሎ ከዳይሬክተር፣ ከህንፃ አገልግሎት ሰራተኛ እና ከ CUPF ጋር ቀደም ተብሎ እንዲመቻች ካልተደረገ በስተቀር ተጠቃሚዎች ከተፈቀዱት ሰአታት በላይ በህንፃው ውስጥ መቆየት አይችሉም። (የተቀመጡት የመጠቀሚያ ሰአታት ገደቦች በምርጫ ተቆጣጥሪዎች ቦርድ ድጋፍ ለሚካሄዱ ምርጫዎች ተግባራዊ አይሆኑም።)

C. ቅፆች

1. የመገልገያ መጠቀሚያ ቅፅ / Facility Use Form (FUF) ማለት የት/ቤት ቦታ ቀን ለመያዝ እና ለወቅቱ ለማስያዝ የተዘጋጀ ቅፅ ነው። ኮንትራት ሲሆን፣ በህዝብ ት/ቤት መገልገያ ውስጥ ለመሆን ለቀረበ የተጠቃሚ ጥያቄ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ቀናትን፣ ጊዜያትን እና ወጪዎችን ዝርዝን የያዘ ነው።

በተጨማሪም በመገልገያው ውስጥ ተጠቃሚው ሙቼ ለመሆን ቀነ ቀጠሮ እንዳስያዘ ለት/ቤቱ ማሳወቂያ ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መጠቀሚያ መስፈርቶችን፣ ሀላፊነቶችን እና ግዴታዎችን ለማወቅ ተጠቃሚዎች እና የት/ቤት ሰራተኞች የቅፁን ጀርባ (እንዲሁም መመሪያዎቹን) ማንበብ አለባቸው።

የት/ቤት ፕሮግራምን የማህበረሰብ አጠቃቀም ሁሉም ተጠቃሚዎች ክፍያ ኖረም አልኖረም የ FUF ቅፅ እንዲሞሉ ያዛል። ተጠቃሚዎች የኦንላይን ማመልከቻዎችን ማስገባት ይችላሉ እና ቀኑ(ቀናቱ) እንደተያዘላቸው የሚያረጋግጥ ፈቃድ ይደርሳቸዋል። ተጨማሪ የሰራተኞች አገልግሎቶች የሚያስፈልጓቸው ከመደበኛ ትምህርት ሰአታት በኋላ የሚካሄዱ የት/ቤት ተግባራት የ FUF ቅፅ መሙላት አለባቸው።

2. የ ሰራተኛ ተጨማሪ ሰአት መጠቀም ፈቃድ ቅፅ (280-19) ለ MCPS ሰራተኞች አገልግሎቶች ICB ክፍያዎች ደቃድ ለመስጠት መሞላት ያለበት በ CUPF በየሳምንቱ የሚለጠፈው “የተፈቀዱ ሰአታት ሪፖርት” ላይ ተጨማሪ ሰአቶቹ ያልተጠቀሱ ከሆነ ነው።

3. የ መሰረዣ/ማሻሻያ ቅፅ የተዘጋጀው በ FUF ሊደረጉ የሚገቡ ማንኛውም ለውጦች ነው። የ FUF ለውጦች በአብዛኛው ሊሆኑ የሚችሉት የተግባር መሰረዞች፣ የተያዘ ጊዜ ማሻሻያዎች፣ ወይም ለተጨማሪ አገልግሎቶች መጠየቂያዎች ናቸው። መጀመሪያ የነበረው FUF ላይ ለውጥ ወይም ማሻሻያ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ፣ የ ICB ቅፅ 23011፡- መሰረዣ/ማሻሻያ ገቢ መደረግ አለበት።

4. የህዝብ ት/ቤቶችን በማህበረሰብ መጠቀምን የሚመለከቱ ጥያቄዎች መቅረብ ያለባቸው ለ CUPF ነው።

D. ክፍያዎች

የ ICB ክፍያ መርሀ ግብር የሚከተሉትን ሁኔታዎች ያካትታል፡-

1. መሰረታዊ መጠን፡- መሰረታዊው ክፍያ ት/ቤቶች ለመጠቀም የሚጠየቀው በሰአት የክፍል ክፍያ ነው ነገር ግን ከመገልገያው፣ በቀን ውስጥ ከተያዘው ሰአት፣ በሳምንቱ ከተያዘው ቀን፣ እና የተግባሩ አይነት አንፃር ይለያያል። ማየት የሚገባችሁ የክፍያ መርሀ ግብር በ ለህዝብ መገልገያዎች የማህበረሰብ አጠቃቀም መመሪያዎች ውስጥ የተጠቀሰውን ነው፣ ለተጠቃሚ ቡድን ተገቢ የሆነውን መሰረታዊ ክፍያ መጠን ለማወቅ መሰረታዊ ክፍያ መጠኑ የሚያካትተው የማሞቂያ እና የአየር ማስተካከያን ነው።

2. የመነሻ አገልግሎት ክፍያ፡- ተጨማሪ ወጥ ክፍያ በሳምንቱ መጨረሻ/እረፍት ቀናት እና በበአላት ለሚጠቀሙ እያንዳንዱ ተጠቃሚ ይጨመራል።

3. **ጂም ሳይጨምር ት/ቤቶች፡- በሳምንቱ መጨረሻ/እረፍት ቀናት እና በበአላት ት/ቤቶች ከጂሞች ውጪ ለመጠቀም ቢያንስ ለሦስት ሰአታት መጠቀም ያስፈልጋል።**

4. ተጨማሪ ክፍያዎች፡- ከመሰረታዊ ክፍያ መጠኑ በተጨማሪ፣ እንደ የህንፃ አገልግሎት ሰራተኛ (BSW)፣ ማዘጋጀት/ማፅዳት፣ የጥበቃ ሰራተኞች፣ የካፍቴሪያ ሰራተኞች፣ የሚዲያ አገልግሎት ቴክኒሽያኖች፣ እና/ወይም የት/ቤት መሳሪያዎችን መጠቀም አይነት አገልግሎቶችን ተጠቃሚ ከጠየቀ ወይም ከፈለገ፣ በሰአት ክፍያ ይከፍላል።

a) የህንፃ አገልግሎት ሰራተኛ (BSW)

የት/ቤት ሰራተኞች ማወቅ ያለባቸው ቢያንስ አንድ የህንፃ አገልግሎት ሰራተኛ (BSW) በእያንዳንዱ መገልገያ ላይ ተገኝቶ ከሰኞ-አርብ የማህበረሰብ ተጠቃሚዎችን ማስገባት እንዳለበት ነው። የማታ ተረኛ የህንፃ አገልግሎት ሰራተኛ (BSW) በማይኖርበት ሁኔታ ውስጥ (በህመም ወይም ከአቅም በላይ በሆኑ ሁኔታዎች)፣ የህንፃ አገልግሎት አስተዳዳሪ (BSW) ወይም ተወካይ የት/ቤት ቦታ ስራዎች (School Plant Operations) ህንፃ አገልግሎት ተቆጣጥሪን በማሳወቅ ተቀያሪ ማግኘት ይገባል። ተቀያሪ ተረኛ የህንፃ አገልግሎት ሰራተኛ (BSW) ማግኘት ካልተቻለ፣ ICB ሰራተኞች ወዲያውኑ እንዲያውቁ መደረግ አለበት።

b) የካፍቴሪያ ሰራተኞች

የጓዳ እቃዎች መጠቀም በተጠየቀ ጊዜ ሁልይ የካፍቴሪያ አስተዳደር ወይም ሰራተኛ ያስፈልጋል። ይሄ መስፈርት ተጠቃሚው ምግብ ማሞቅ ብቻ እንኳን ቢፈልግ መሟላት አለበት።

c) የተለየ መሳሪያ ጥቅም ላይ ሲውል፣ ብቃት ያለው አስተማሪ ወይም የሚድያ አገልግሎቶች ቴክኒሺያን (MST) መኖር አለበት።

በተግባሩ እና በመሰራሪያው ፍላጎቶች መሰረት፣ በዳይሬክተር ከተፈቀደ የተማሪ እረዳት ሊመደብ ይችላል። በተግባሩ እና በመሰራሪያው ፍላጎቶች መሰረት፣ በዳይሬክተር ከተፈቀደ የተማሪ እረዳት ሊመደብ ይችላል።

d) መሳሪያዎች

የት/ቤት መሳሪያዎችን መጠቀም በግልፅ ተከልክሏል፣ ይሄም ቀደም ብሎ ፈቃድ ከተሰጠ እና ከዳይሬክተር ወይም ከእሱ/ከእሷ ተወካይ ጋር ለመሳሪያዎቹ አስፈላጊውን ደህንነት እና ጥበቃ ለማቅረብ ነገሮች ካልተመቻቹ በስተቀር ነው።

የ MCPS መሳሪያዎችን ለመጠቀም ሲጠየቅ፣ እንደ የድምፅና ምስል፣ የልዩ መብራት፣ ወይም ሌላ ቁሳቁሶች (የሚያልቁ የእቃ ክፍሎቹን ለመቀየር ካስፈለገ)፣ በሰአት የመሳሪያዎች መጠቀሚያ ክፍያ ይሰላል። ይሄ ክፍያ፣ የሚያልቁ እቃዎችን ለመቀየሪያ ሊውል የሚችል፣ የሚከፈለው ለ CUPF እና በእየ ሩብ አመት ለሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች እና በአመት አጋማሽ ደግሞ ለአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች መልሶ ይከፈላል። የት/ቤት መሳሪያዎችን ለመጠቀም የ MCPS ሰራተኞች ተጨማሪ ሰአት የሚያስፈልግ ከሆነ፣ ይሄ አገልግሎት በ FUF ክፍያ ዝርዝር ውስጥ ይካተታል። በተጠቃሚ ቡድን የተበላሸ ማንኛውም የህዝብ ት/ቤት መሳሪያዎች የጥገና ወይም የመቀየሪያ ክፍያ የተጠቃሚ ቡድኑ ሀላፊነት ነው። በተጠቃሚ ለተግባር ተብሎ ለመጣ ማንኛውም የት/ቤት ያልሆነ መሳሪያ MCPS ወይም ICB ሀላፊነት አይወስዱም።

E. የት/ቤት መዘጋቶች

1. ት/ቤቶች ቀደም ብለው ከተዘጉ ወይም ሙሉ ቀን ከተዘጉ፣ ማንኛውም በት/ቤት ስፖንሰር ያልተደረጉ ተግባራት ወዲያውኑ ይሰረዛሉ።

2. በሳምንቱ መጨረሻ/እረፍት ቀናት እና በበአላት፣ የት/ቤት መገልገያዎችን ቀደም ብሎ የመዝጋት፣ መክፈቻን የማዘግየት፣ ወይም ቀኑን ሙሉ የመዝጋት ውሳኔ የሚሰጠው በ CUPF ከዋና ስራ አስተዳደር ቢሮ ጋር በመመካከር ነው። CUPF ማንኛውንም የመሰረዝ መግለጫዎች በተመለከት ጠዋት 7:00 a.m. ለአካባቢው ሚድያ ያሳውቃል።

3. ት/ቤቶች ለውጪ የማህበረሰብ ጥቅም በ ICB ሲዘጉ፣ የማህበረሰብ ተግባራት ክፍያቸው ተመላሽ እንዲደረግላቸው መብት አላቸው።

   የፕሮግራሙን ምንነት ለሁሉም ተሳታፊዎች ለማሳወቅ የመሞከር ሀለፊነት የእያንዳንዱ ተግባር ስፖንሰር አድራጊ ይሆናል።

F. የአጠቃቀም ሁኔታዎች

የመገልገያ አጠቃቀም ቅፆች የሚወክሉት በተጠቃሚ እና በሞንጎመሪ ካውንቲ መካከል የአለን የኮንትራት ስምምነት ነው። በማዕከላዊ የጊዜ መርሀ ግብር ማውጣት ስር ለሚገኙ ሁሉም ት/ቤቶች፣ ኮንትራቶቹ የሚፈረሙት በሁለቱም በ CUPF እና በተጠቃሚ ቡድኖች ነው። የት/ቤት የጊዜ መርሀ ግብር አውጪዎች እና የህንፃ አገልግሎት አስተዳደሮች በት/ቤቶቻቸው ጊዜ የተመደበላቸውን ተግባራት በሚመለከት ከክፍል የመረጃ ቋት (Class database) በየጊዜው የተሻሻለውን መረጃ በቋሚነት መውሰድ አለባቸው። ኮንትራቶች አንዴ ከተፈረሙ በኋላ፣ የሚከተሉት ህጎች ተግባራዊ ይሆናሉ፦

1. የት/ቤት ቦታው ለተጠቃሚው ተመድቧል እና ከተጠቃሚው ፈቃድ ውጪ ሊቀየር ወይም ሊሻሻል አይችልም፣ ድንገተኛ ሁኔታዎች ካልተፈጠሩ በስተቀር።

2. የተጠቃሚው ተግባር የሚሆነውም፦

   a) ስርአቱን የጠበቀ እና ህጋዊ

   b) ብጥብጥ የሚያስነሳ ወይም የት/ቤት መገልገያዎች ወይም መሳሪያዎች ላይ ጉዳት የሚያደርስ ተፈጥሮ የሌለው

   c) በዘር፣ በሀይማኖት፣ በፆታ ወይም በቀለም ምክንያት የሚከለክል ያልሆነ

3. የሚከተሉት ነገሮች በሁሉም ጊዜያት በት/ቤት ህንፃዎች ላይ እና በት/ቤት ቦታዎች ላይ የተከለከሉ ናቸው፦

   a) የአልኮል መጠጦችን ወይም ሌላ አስካሪዎችን መጠቀም ወይም መያዝ

   b) ቁማር በ ሜሪላንድ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አባሪ ኮድ ርዕስ 13፣ ንዑስ ርዕስ 18 ተገቢ ከሆነ ህጋዊ ፈቃድ እና/ወይም ፈቃዶች ጋር ከተፈቀደው ውጪ

   c) የት/ቤት ጅምናዚየሞችን በቤት ውስጥ ለእግር ኳስ፣ ለኳስ ጨዋታ፣ ለላክሮስ፣ ለሆኪ፣ ለክሪኬት፣ ከቤዝ ቦል/ለሶፍት ቦል መጠቀም

d) ማጨስ ወይም የስጋራ ምርቶችን መጠቀም

e) እሳቶች፣ መጥበስ፣ ክፍት ነበልባል እሳት፣ እና የሚቀጣጠሉ እቃዎችን መጠቀም፣ ከቤት ውጪ በከሰል መጥበስን አይጨምርም ምክንያቱም በልዩነት በተናጠል በየት/ቤቱ ሊፈቀድ ይችላል የሜዳውን-መከራየት (Adopt-a-Field) ስምምነትቶች አካል ሆኖ

f) በተፈጥሯቸው ግላዊ የሆኑ ፓርቲዎች/ዝግጅቶች እና ክብረ በአላት፤ ይሄ ክልከላ የሚያካትተው ልደት፣ አመታዊ በአል፣ የጋብቻ ስነ-ስርዓቶች፣ እና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባሮችን ነው

g) የጦር መሳሪያዎች፣ የእጅ መሳሪያዎች፣ ጥይቶች

h) ከልክ ያለፈ ጫጫታ

4. ምንም አይነት ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ምልክቶች፣ ባነሮች፣ በንዲራዎች ወይም ተመሳሳይ ነገሮች በት/ቤት ህንፃዎች ውስጥ ወይም ላይ ወይም የት/ቤት ሜዳዎች ላይ በማንኛውም ቡድን መቀመጥ አይችሉም በትምህርት ቤቱ ወይም በትምህርት ቤት PTA ስፖንሰር ከተደረጉ እንቅስቃሴዎች በስተቀር ከሚከተሉት ሁለት ልዩ ሁኔታዎች ጋር፦

a) በተቆጣጣሪዎች ቦርድ ለምርጫዎች በት/ቤቶች ውስጥ የሚደረጉ ተግባራት ከዚህ እገዳ ነፃ ናቸው።

b) ሌላ ቡድኖች፣ እንደ ቤተ-ክርስቲያናት፣ ት/ቤቶች የሚጠቀሙ፣ ጊዜያዊ የመለያ ምልክቶችን በት/ቤት ሜዳዎች ላይ ት/ቤቱን በሚጠቀሙበት በትክክለኛው ሰአታት ላይ ብቻ ማስቀመጥ ይችላሉ። ት/ቤቱ መጠቀም በሚያበቃበት ጊዜ ቡድኑ ምልክቶቹን ማንሳት አለበት።

5. ከውጪ በመጣ ድርጅት ህንፃዎች ጥቅም ላይ መዋል በምንም መልኩ በመደበኛ የትምህርት ሰአታት የሚደረግ መደበኛ የትምህርት ፕሮግራምን አግገድብም ወይም አያግድም።

6. የት/ቤት መገልገያዎች ለዳንስ መጠቀም የሚቻሉት የሚከተሉት ቡድኖች ብቻ ናቸው፦

a) የፐብሊክ/የህዝብ ት/ቤት ቡድኖች

b) የተደራጁ የመዝናኛ አዘጋጅ ክፍሎች እና የቤተሰብ-አስተማሪዎች ማህበራት፤ ነገር ግን፣ ቡድኖቹ መገልገያዎቹን ከአጠቃቀማቸው የተነሳ ለሚከሰሩ ማንኛውም መበላሸቶች ወይም ጉዳቶች የገንዘብ ክፍያ ሀላፊነቶችን ይወስዳሉ

7. የ ICB አላማ የት/ቤት መገልገያዎችን ማህበረሰቡ በከፍተኛ ደረጃ መጠቀሙን ማበረታታት እና ማመቻቸት ነው። ነገር ግን፣ ICB ማንኛውም የት/ቤት መጠቀም ጥያቄዎችን የመመርመር መብትን ይይዛል።

8. በቋሚነት የት/ቤት ህንፃን በማንኛውም ቡድን መጠቀም የሚመረከዘው በት/ቤት አጠቃቀም ደንቦች ላይ ነው። ሁሉም ተጠቃሚዎች የት/ቤት ንብረቶችን ለመጠበቅ እና የህዝብ ደህንነትን ለማረጋገጥ ሁሉንም አስፈላጊ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው።

ዳይሬክተሩ/ሯ መገልገያዎች በማንኛውም ቡድን አግባብ በሌለው መልኩ ጥቅም ላይ እንደዋሉ ከተሰማው/ት፣ በፅሁፍ ለ CUPF ማሳወቅ አለበት/ባት። ቀጣይነት ያለው አግባብ በሌለው መልኩ መጠቀም የህንፃ መጠቀም ኮንትራት መሰረዝን ሊያስከትል ይችላል። የት/ቤት ንብረትን ያለአግባብ የሚጠቀሙ ወይም በማንኛውም መልኩ ደንቦችን የማያከብሩ ወይም ለህዝብ አሳሳቢ ሁኔታ የሚፈጥሩ ወይም የሚያበላሹ ተጠቃሚ ቡድኖች ወደ ፊት ከመጠቀም ሊታገዱ ይችላሉ።

9. ማንኛውም የት/ቤት ንብረትን የሚጠቀም ቡድን ወይም ድርጅት የመገልገያ አጠቃቀም ስምምነትን ማስፈፀም ይጠበቅበታል። ይሄ ስምምነት ተጠቃሚዎች ተግባራቶቻቸውን በትምህርት ቦርድ ፖሊሲ መሰረት እንዲያከናውን እንዲጠበቅባቸው ያደርጋል። በተጨማሪም፣ ይሄ ስምምነት የትምህርት ቦርድ፣ ግንኙነት ያላቸው ግለሰብ አባላት፣ እና ማንኛውም የ MCPS ሰራተኞችን ለመጥፋት፣ ለመጎዳት፣ ለመበላሸት፣ ይገባኛሎች፣ ያልተሟሉ ነገሮች ወይም ተዛማጅ ወጪዎችን በተመለከት ተጠያቂ እንዳይሆኑ፣ ተጠቃሚዎች እንዲጠብቋቸው እና እንዳይጎዱ እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል፣ ይሄም ከእነሱ የመገልገያ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚመጣ ምክንያታዊ የሆነ የጠበቃ ክፍያዎችን ያካትታል። ከውጪ በመጣ ቡድን የመገልገያ አጠቃቀም የተነሳ የ MCPS ንብረት ላይ ኪሳራ በሚደርስበት ወቅት፣ የጉዳቱ መጠን በ MCPS ከ CUPF ጋር በመመካከር ይወሰናል፣ እና በዚሁ መሰረት ተጠቃሚ ቡድኑ ክፍያውን እንዲፈፅም ይደረጋል።

10. በማንኛውም ቡድን የት/ቤት ህንፃን መጠቀም ከውጪ ለመጣው ቡድን ጥቅም ሲባል አቅርቦቶችን እና/ወይም መሳሪያዎችን መቀበልን እና/ወይም ማስቀመጥን የሚያካትት ከሆነ፣ ይሄ ሁኔታ የማመልከት ሂደቱ ክፍል ሆኖ መካተት አለበት። እነዚህ አቅርቦቶች እና/ወይም መሳሪያዎች በት/ቤት በተቀመጡበት ወቅት ለሚደርስ ኪሳራ ወይም ጉዳት MCPS ወይም ICB ሀላፊነት አይወስዱም።

ስለ ደንቡ ታሪክ፦ አዲስ ደንብ፣ ኦክቶበር 1982፤ የተሻሻለ አፕሪል 1989፤ የተሻሻለ አፕሪል 24፣ 2003፣ የተሻሻለ ፌብዩዋሪ 3፣ 2006።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

<table>
<tr><td>MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td><td>MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*</td></tr>
<tr><td>Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org</td><td>Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td>በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td><td>በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ</td></tr>
<tr><td>Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org</td><td>ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org</td></tr>
<tr><td colspan="2">"Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org</td></tr>
</table>

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org